# ርእሰ አንቀጽ

*ነሐሴ/መስከረም (98'/99')*

# መልካም አዲስ ዓመት!

እነሆ መስከረም ጠባ፥ አዲስ ዓመት መጣ። እንደ አባትአደሩ፥ ዕንቁጣጣሽ፥ መልካም አዲስ ዓመት የሚል ተስፋ እንለዋወጥ። ልዩው የኢትዮጵያ ታሪክና ባህል የራሱን የጊዜ ሰንጠረዥ ቆጥሮ ፲፱፻፺፱ (1999) ብሏል። በኢትዮጵያዊያን የዘመን ቅመራ ታሪክ አቆጣጠር ወደ አዲሱ ሺህ ዘመን ለመሸጋገር ተንግዲህ የወራት ፍሬዎች ይቀሩናል።

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ያለፉትን 2ሺህ ዘመናት አብረው አልፈውባቸዋል። በነዚህ ዘመኖች ውስጥ የመጡና ያለፉ ሀገሮችና አዳዲስ ወሰኖች ፈጥረው የኖሩ ሕዝቦች እንዳሉና እንደነበሩ ቢታወስም፥ ኢትዮጵያና ሕዝቧ ግን ከህብረተሰብ ሥርዓተ መንግስት አጀማመር ተነስተው የደግና የመከራ ዘመናትን አስቆጥረው ዛሬ ድረስ አሉ። የአዲሱን ሺህ ዘመን ዋዜማ የምንቀበለው በተስፋ ቢሆንም፥ ለኢትዮጵያና ሕዝቧ ቀጣይ ታሪክ ማስተማመኛው ግን፥ በእጃችን ላይ ያለ መሆኑን በመገንዘብ ነው። የኢትዮጵያ ያለፈ ረጅም ታሪክ ፥ በጎውም ይሁን መጥፎው፥ ብዙው እጅ የሕዝቧ ድርጊት ውጤት ነው። ታሪካችን በቀደምትነቱ የተፈጥሮ መሠረት ያለውና፥ ለተከተለው እያሌ የህብረተሰብ ውስብስብ ግንኙነትና ልውውጥ ታሪክም፥ መመርመሪያ የመሆኑን ያህል፥ በብዙ ነገሮች የተለየ ነውና፥ ይህን የማንነት ሥንክሣር ጠብቆ ለማኖርም፥ ብዙ ዋጋ የጠየቀ ነው። የሰው ልጅ እንደዛሬው መሬትን ሳይሞላና፥ ሥጋዊ ፍላጎቱን ለማሟላት ውቅያኖስ ከሰማይ ሳይሰነጥቅ፥ የነበሩ ታላላቅ ፈላስፋዎችና የሃይማኖት መሪዎች ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የሚገባውን ክብር ሰጥተው ይመለክቱ ነበር። ይሁን እንጅ ምድር ገና ሳትጠብና ሲሳይዋ ሳያጥጥ፥ ከወቅታዊ ሁለገባዊ ጠቀሜታ አልፎ ማጋበስና ማካበት የተመኘው የሰው ልጅ የፍላጎት ምዝግዝግ፥ ኢትዮጵያ ላይ በመቃጣትና በመጥለፍ፥ ሕዝቧን በመከላከል አጣብቂኝ ሰቅዞ ይዞ ለዘመናት ማንኳተቱና ማስዳሁ እውነት ነው።

ከታሪካችን እንደምንማረው ሁሉ፥ ኢትዮጵያ ለአያሌ ብዙ ዘመናት ራሷን ለመከላከል በወሰደችው እርምጃ፥ ከውጭው ዓለም ጋር ተቆራርጣና ከሁሉም ነገር ራስዋን ከልላ መኖሯ፥ ቢያንስ በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ተጎድታለች ማለት ይቻላል። ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ፥ ከሰፊው ዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ጋር በፈጠራና በመረጃ ልውውጥ መወዳደርና የዕድገት አድማስን ለማስፋት አለመቻሏ ሲሆን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፥ በየጊዜው የተፈራረቁባትን አድሃሪና ጨቋኝ መሪዎችን ከውጭ ለሚቃጡ አደጋዎች ሁሉ እንደ ደህንነት ዋስትና በማየት፥ በደላቸውን መቻልና እልፎም ከእግዚአብሔር እንደሰጡ ስጦታዎች በመቁጠር፥ አምርረው እንዳይታገሏቸው ተጽእኖ ፈጥሮባቸዋል። ጨቋኝ መሪዎች ይህን ተጠቅመው፥ ለሕዝቡና ለሀገሪቱ ደህንነት የተመረጡ አስመስለው፥ ራሳቸውን ወደ ፈጣሪ በማስጠጋት፥ የበደልንና የግፍን ጽዋ፥ "ይታደሉታል እንጅ አታገሉትም" ብለው መሰየማቸውንም በታሪካችን ምእራፍ ላይ ልንመለከተው የምንችለው ነው። ይህ ሰይጣናዊ የሆነ፥ "ልንገዛችሁ ተሰጠናችሁዋል" አይነት የገዥዎች ሰበካ እየሰረጸ፥ ሕዝባችን በእድሉ እንዲያማርና፥ ጀርባውን አጉብጦ ተሸክሞ እንዲኖር አስተዋጽኦ አድርጓል።

“ሰማይ አይታረስም፥ ንጉስ አይከሰስም” የሚል ይትባህል፥ በመልቲ ስብከታቸው ያጠነጠኑት ጨቋኝና ሁዋላ ቀር መሪዎች፥ ሁዋላ ሁዋላ የዘመናዊ ትምህርት እውቀት ቀስመው አይናቸውን በከፈቱ የሀገሪቱ ወጣት ልጆች፥ በሰማይ ላይ መብረር መቻሉን፥ ንጉሥንም በጥፋቱ መቃወምና በፍትሃዊ ፍርድም መቅጣት መቻል ብቻ ሳይሆን፥ የዜግነት ግዴታም መሆኑን በመግለጽ፥ ፈንቅለው ወጡ። በተጧጧፈ ሕዝባዊ ትግልም ገባሩንና አማኙን የኢትዮጵያ ሕዝብ በማሳተፍ፥ ያን “ተጨፈኑ እናሞኛችሁ” የጭቆና ሥርዓት ሰባብረው ቢጥሉትም፥ በሚያሳዝ ን ሁኔታ ግን ሳት በላሱ አፈጮሌዎችና ደም እንደጎርፍ በሚያፈሱ አምባገነኖች ተተካ። ይሁን እንጅ፥ ከተራማጅ ወጣት ልጆቹ ጎን ተሰልፎ ሲታገል አይኑ ሞራው የተገለጠለት የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በንጉሣዊው ሥርዓት ሥር የተተካውን ወታደራዊ አምባገነን መንግሥት፥ ባመቸው መንገድ ሁሉ ታግሎ ያሸነፈው መሆኑ ሲዘገብ፤ ዛሬም ገና መራር ትግል አለበት። የዛሬው ትግሉ በጠባብ ትምክህተኝነት፥ በዘረኝነትና በከፋፋይነት ላይ ያነጻጸረ ነው። የትግሉ ዒላማ በቅርበትና በጉልህ የሚታይ በመሆኑ ፥ ተለማማጅ ተኳሽ እንኳ አይስተውም ተብሎ ቢገመትም፥ እስካሁን መትቶ መጣል አልተቻለም። ለዚህ ዋናው ምክንያት ሌላ ሳይሆን፥ በሕዝብ ልጆች መካከል ህብረትና ትብብር መጥፋቱ የችግሩ ብልት ነው።

እናም ይህ አዲስ አመት የወያኔ/ሕወሃት'ን አረመኔያዊና ፋሽስታዊ መንግሥት ተባብሮ ለመታገልና፥ በአሸናፊነት የምንወጣበት እንዲሆን ሁላችንም ልንመኝና በተግባር ልንሳተፍ ይገባል። የእድገትና ብልጽግና ጎዳና በሰላም አምባ ያልፋልና፥ የሰላሙ አምባ የዛሬ ዓመት በአበባዎች ፈክቶ ከፍ ብሎ እንዲታይ፥ ካለፉት ብዛት ያላቸው ድክመቶቻችንና ጎደሎዎቻችን ተምረን፥ ለብሩህ ተስፋ በአንድነት እንትመም። በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ሚናችንን በአግባቡ ተረድተን የምንችለውን አስተዋጽኦ ማድረግ ስለሚጠበቅ፥ ሕዝባችንን በብቃትና በቆራጥነት መርተው ለድል የሚያበቁትን ከመደገፍ ወደሁዋላ አንበል።
እንቁጣጣሽ!! መልካም አዲስ ዓመት ለሕዝባችንና ለሀገራችን ኢትዮጵያ ይሁን።